በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁ. 200564

ቀን ፡- ሕዳር 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች ፡- የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ ጥበበ መኮንን - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ የጆቴወርቅ ኪዳኔ

2. አቶ ሚሊዮን ቅጣው

3. አልማዝ ቅጣው

4. ወርቅነሽ ቅጣው

5. መንበረ ቅጣው

6. ሔለን ቅጣው

7. ዮዲት ቅጣው

8. ምሥራቅ ቅጣው

ይሕ መዝገብ ከሰበር መዝገብ ቁጥር 204121 ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ የውል አለመፈጸምና የኪሣራ አከፋፈልን የተመለከተ ክርክር ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች ከሳሽ ሲሆን ተጠሪዎች ተከሳሾች ነበሩ፡፡ አመልካች ግንቦት 04 ቀን 2009 ዓ/ም በተጻፈ የክስ ማመልከቻ ያቀረበው ክስ የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና ከ2ኛ-8ኛ ተጠሪዎች አባት የሆኑት አቶ ቅጣው መሸሻ ከአመልካች ጋር በተደረገ የንግድ ቤት ኪራይ ውል በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 05 ቀበሌ 12 የቤት ቁጥሩ 1165 የሆነ የንግድ ቤት በወር ብር 212.50 እየከፈሉ ከ1969 ዓ/ም እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስ እየከፈሉ ሲጠቀሙበት ቆይተው የተከራዩትን ቤት ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ ከአከራዩ ዕውቅና ውጪ ለሦስተኛ ወገን አከራይተው የማይገባ ጥቅም በማግኘታቸው ምክንያት አመልካች የኪራይ ተመኑን በማስተካከል በወር ብር 31,479.00 እንዲከፍሉ አድርጓል፡፡ አቶ ቅጣው ቅሬታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ በዚህ መካከል አቶ ቅጣው መሸሻ ውል ሳያድሱ ሕዳር 13 ቀን 2005 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ውል ያላደስነው ባለቤቴ ሕመም ላይ ስለቆየና ሞግዚትነትና ወራሽነት እስከምናረጋግጥ ድረስ ስለሆነ ጊዜ እንዲሰጠን በማለት በጽሁፍ አመልክተዋል፤ ውዝፍ ዕዳውን በተመለከተ የአንድ ዓመት የመክፈያ ጊዜ እንዲሰጣቸው ጠይቀው ከአመልካች ጋር የውል ሥምምነት አድርገዋል፡፡ በሥምምነቱ መሠረት ዕዳውን መክፈል ጀምረው ያቋረጡ ሲሆን እስከ ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም ድረስም ሲገለገሉበት ቆይተዋል፡፡ ስለሆነም የኪራይ ገንዘብ ብር 2,311,503.59 ተጠሪዎች ከወለድ ጋር እንዲከፍሉ ሲል ዳኝነት ጠይቋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ በፍ/ሕ/ቁ. 2024(መ) መሠረት ከሁለት ዓመት በላይ የተጠራቀመ የቤት ኪራይ ክፍያዎችን አመልካች የመጠየቅ መብቱ በይርጋ የታገደ ነው፣ በንግድ ቤት ያለኝ መብትና ግዴታ በሌላ የፍርድ ቤት ክርክር የተወሰነ በመሆኑ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው፣ የንግድ ድርጅቱ የባለቤቴ የግል ሀብት ነው ስለተባለ 1ኛ ተጠሪ ክፍያው አይመለከተኝም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ በፍሬ ነገሩም የኪራይ ዋጋ ብር 31,479.00 እንዲሆን የተደረገ ሥምምነት የለም፡፡ መክፈል ካለብኝ እንኳን በብር 212.50 ሂሳብ ነው፡፡ ሟች ባለቤቱ ሳይዋዋል ነው የሞተው፤ ባለቤት ከሞተ በኋላ ሟች ትክክለኛ ኪራይ ለማስከፈል የጀመረውን ክርክር ለማስቀጠል በ10/05/2005 ዓ/ም እና በ08/08/2005 ዓ/ም ለአመልካች ጥያቄ አቅርቤያለሁ፡፡ ከአመልካች ጋር በ09/08/2005 ዓ/ም ያደረግሁት ሥምምነት ንግዱ ወደኪሣራ እንዳይገባ በማሰብ አለ የተባለው ብር 547,287.13 ዕዳ በከፊል ከፍዬ ቀሪው ደግሞ ንግዱን እያንቀሳቀስኩኝ ለመክፈል የታለመ ነው፡፡ በውሉ መሠረት ብር 200,000.00 ከከፈልኩኝ በኋላ ቀሪዎቹ ተጠሪዎች ባለመፍቀዳቸው ንግድ ቤቱ አስተዳዳሪ ተመድቦለት አስረክቤያለሁ፡፡ ከዚህ በኋላም ከንግዱ ምንም ዓይነት ጥቅም አላገኘሁም፡፡ በውሉ መሠረት የቅጣት ክፍያ 10% ሊያስከፍል የሚችለው ኪራይ የዘገየባቸውን የመጀመሪያ

ስድስት ወራት ብቻ ነው፤ በውሉ አንቀጽ 3(3) መሠረት ከስድስት ወር በላይ ክፍያ ቢዘገይ ውሉን የመሠረዝ መበት አመልካች አለው፡፡ ከስድስት ወራት በላይ ላለው ጊዜ ቅጣት ልከፍል አይገባም ብለዋል፡፡

ከ2ኛ-8ኛ ያሉት ተጠሪዎች በበኩላቸው ሟች አባታችን ከሕግ ውጭ አከራይቷል መባሉ በማስረጃ ያልተረጋገጠ ነው፤ የኪራይ ጭማሪ ተደርጓል የተባለውም የተጋነነ እና እኛን የማያስገድድ ነው፡፡ ከተገደድንም በውሉ መሠረት ብር 212.50 ወርሃዊ ሂሳብ ብቻ ነው፡፡ ሟች ከሞተ አንስቶ በንግድ ቤቱ ፈቃድ በማሳደስ ሲጠቀሙበት እና ሲሰሩበት የነበሩት 1ኛ ተጠሪ እንጂ ከ2ኛ-8ኛ ያለነው ተጠሪዎች ባለመሆናችን ለዕዳው ኃላፊነት የለብንም፡፡ ውል ሳንገባ ወራሽ በመሆናችን ብቻ ለዕዳው ልንጠየቅ አይገባም፡፡ አመልካች ጻፍኩት ያለው የማስጠንቀቂያ ደብዳቤዎች ለእኛ አልደረሰም፡፡ አመልካች የንግድ ቤቱን ተረከብን በማለት በጽሁፍ አሳውቀነዋል፡፡ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ውድቅ ካደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ከ2ኛ - 8ኛ ያሉት ተጠሪዎች በንግድ ቤቱ ላይ ወራሽነት ቢያረጋግጡም በንግድ ቤቱ ባለመጠቀማቸው ኃላፊነት የለባቸውም፡፡ 1ኛ ተጠሪ በአዲስ ክፍያ ለመክፈል ተስማምተው መክፈልም ጀምረዋል፡፡ ስለሆነም ቀሪውን ዕዳም የመክፈል ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ ከሚያዚያ 01 ቀን 2004 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም ድረስ ያለውን የ57 ወራት ብር 1,780,137.93 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች ይክፈሉ፤ የውል ቅጣትን በተመለከተ አመልካች ከስድስት ወር በኋላ ውል መሠረዝ እየቻለ ያልሰረዘ በመሆኑ ከስድስት ወራት በላይ ላለው ቅጣት 1ኛ ተጠሪ ሊከፍሉ ስለማይገባ የስድስት ወር ቅጣት ብር 18,887.40 ብቻ የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው፤ በአጠቃላይ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር ብር 2,066,045.33 1ኛ ተጠሪ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ሆነ 1ኛ ተጠሪ በተለያዩ መዝገቦች ያቀረቡትን ይግባኝ ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የኪራይ ውሉ ያልተቋረጠው 1ኛ ተጠሪ በተለያዬ ጊዜ ውሉ እንዳይቋረጥ እና ዕዳውን ለመክፈል ጊዜ እንዲሰጣቸው በመጠየቀቻውና መክፈልም በመጀመራቸው ነው፡፡ ቅጣት ብር 264,344.97 ሊከፈል ይገባል፡፡ ከ2ኛ - 8ኛ ተጠሪዎች በንግድ ቤቱ መጠቀም አለመጠቀማቸው ሳይሆን የሟች አባታቸውን ዕዳና መብት ስለሚወርሱ ነው ክሱ የቀረበው፤ በግልጽ ውርሱ ተጣርቶ አንወርስም አላሉም፤ ወራሽ በመሆናቸው ለዕዳው ኃላፊ ናቸው ሊባል ይገባል የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ከ2ኛ - 8ኛ ድረስ ያሉት ተጠሪዎች በፍርድ ቤት ክርክር የንግድ ቤቱ ወራሽ መሆናቸው በተገለጸበት ሁኔታ ለዕዳው ኃላፊነት የለባቸውም መባሉ ሕጋዊነቱን ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርብ በማዘዙ 1ኛ ተጠሪ በውሉ ኪራይ ካልተከፈለና ከስድስት ወራት በኋላ ውሉን የመሠረዝ መበት እንዳለው ተመልክቷል፤ ባለመሰረዙ ምክንያት ከስድስት ወራት በኋላ ያለውን ቅጣት ሊጠይቅ አይችልም ብለዋል፡፡ ከ2ኛ - 8ኛ ያሉት ተጠሪዎች በበኩላቸው የአባታችን ወራሽ በመሆናችን ብቻ ልንጠየቅ አይገባም፤ የኪራይ ውል አልተዋዋልንም፣ የንግድ ቤቱን እንድንረከብ ሆነ እንድንጠቀም አልተደረገም፣ ስለሆነም ለዕዳው ተጠያቂነት የለብንም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

1ኛ ተጠሪ በሰበር መዝገብ ቁጥር 204121 አመልካች ላይ ያቀረቡት የሠበር አቤቱታ ይዘት ደግሞ በፍ/ሕ/ቁ. 2024(መ) መሠረት ከሁለት ዓመት በላይ የተጠራቀመ የቤት ኪራይ ክፍያዎችን አመልካች የመጠየቅ መብቱ በይርጋ የታገደ ነው፣ በንግድ ቤት ያለኝ መብትና ግዴታ በሌላ የፍርድ ቤት ክርክር የተወሰነ በመሆኑ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው፣ የንግድ ድርጅቱ የባለቤቴ የግል ሀብት ነው ስለተባለ ክፍያው አይመለከተኝም፤ የንግድ ቤቱን ውርስ አጣሪ እያስተዳደረው ስለመሆኑና በንግድ ቤቱ ላይ መብት እንደሌለኝ የሚያስረዱ መዝገቦችን የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃነት አስቅርቦ አለመመርሩ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የተሻሻለ የኪራይ ውል ሆነ የኪራይ ዋጋ የለም የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የንግድ ቤት የሟች የግል ሀብት ነው ተብሎ በተወሰነበት ሁኔታ 1ኛ ተጠሪ የቤት ኪራይ እንዲከፍሉ የተወሰነበት አግባብነትን ለማጣራት አመልካች መልስ እንዲያቀርብ የታዘዘ ሲሆን አመልካች ያቀረበው መልስ ይዘት 1ኛ ተጠሪ ዕዳው መኖሩን አምነው በአዲስ የኪራይ ዋጋ ለመክፈል የውል ሥምምነት ከማድረጋቸውም ባሻገር ክፍያ የጀመሩ በመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 2024(መ) መሠረት በይርጋ ሊታገድ አይችልም፡፡ በ1ኛ ተጠሪ እና ከ2ኛ-8ኛ ድረስ ባሉት ተጠሪዎች መካከል የውርስ ሀብት ክርክር ተደርጎ መወሰኑ አመልካች ካቀረበው ክስ ጋር የሚገናኝ ባለመሆኑ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ሊባል አይገባውም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ሟች ባለቤት በመሆናቸውና በንግድ ቤቱም በጋራ ሲጠቀሙ የነበረ፣ ባለቤታቸው ከሞቱ በኂላም መጠቀም የቀጠሉ ስለሆነ ዕዳው ለትዳር ጥቅም የዋለ በመሆኑ ኃላፊ መባላቸው ተገቢ ነው፡፡ የንግድ ቤቱ የግል ሀብት ነው ተብሎ የተወሰነው ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ/ም ሲሆን አመልካች እንዲከፈለው የጠየቀው ዕዳ ከሚያዚያ 01 ቀን 2004 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም ድረስ ስለሆነ ክፍያውን የማይከፍሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ አመልካች ተቋም እንደመሆኑ መጠን የኪራይ ተመን ሲያሻሻል ከተከራይ ጋር ሥምምነት ማድረግ እንደማይጠበቅበት ሕጉ ይደነግጋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በገቡት የውል ግዴታ መሠረት የተወሰነ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ተጨማሪ ማስረጃ አስቀርቦ የሚመረምርበት አግባብ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ 1ኛ ተጠሪ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘውን ጭብጥ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ግንቦት 04 ቀን 2009 ዓ/ም በተጻፈ የክስ ማመልከቻ ያቀረበው ክስ የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና ከ2ኛ-8ኛ ተጠሪዎች አባት የሆኑት አቶ ቅጣው መሸሻ ከአመልካች ጋር በተደረገ የንግድ ቤት ኪራይ ውል በአዲስ አበባ ከተማ  በቀድሞ ወረዳ 05 ቀበሌ 12 የቤት ቁጥሩ 1165 የሆነ የንግድ ቤት የተከራዩ ሲሆን ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ ከአከራዩ ዕውቅና ውጪ ለሦስተኛ ወገን አከራይተው የማይገባ ጥቅም በማግኘታቸው ምክንያት አመልካች የኪራይ ተመኑን በማስተካከል በወር ብር 31,479.00 እንዲከፍሉ አድርጓል፡፡ አቶ ቅጣው ቅሬታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ በዚህ መካከል አቶ ቅጣው መሸሻ ውል ሳያድሱ ሕዳር 13 ቀን 2005 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ ስለሆነም የሟች ባለቤት የሆኑት 1ኛ ተጠሪ በገቡት የውል ሥምምነት መሠረት እና ከ2ኛ-8ኛ ያሉት ተጠሪዎች ወራሽ በመሆናቸው ከሚያዚያ 01 ቀን 2004 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም ድረስ ያለውን የኪራይ ገንዘብ ከነቅጣቱ ብር

2,311,503.59 እንዲከፍሉ የሚል ሲሆን ተጠሪዎች በፍ/ሕ/ቁ. 2024(መ) መሠረት ከሁለት ዓመት በላይ የተጠራቀመ የቤት ኪራይ ክፍያዎችን አመልካች የመጠየቅ መብቱ በይርጋ የታገደ ነው፣ 1ኛ ተጠሪ በንግድ ቤት ያለኝ መብትና ግዴታ በሌላ የፍርድ ቤት ክርክር የተወሰነ በመሆኑ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በሥረ-ነገሩም ለኪራይ ገንዘቡ ኃላፊ አይደለንም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪዎች የፍ/ሕ/ቁ. 2024(መ) መሠረት በማድረግ ከሁለት ዓመት በላይ የተጠራቀመ የቤት ኪራይ ክፍያዎችን አመልካች የመጠየቅ መብቱ በይርጋ የታገደ ነው በሚል ያቀረቡትን መቃወሚያ ስንመርምር ድንጋጌው መብትን አስመልክቶ ክስ የማቅረቢያ ጊዜን ቀሪ የሚያደርግ የይርጋ ጽንሰ ሃሳብ ያለው አይደለም፡፡ በክርክር ሂደት ፍሬ ነገሮችን ማረጋገጥ የሚቻልባቸው ዘዴዎች ማስረጃ፣ በፍርድ ቤት በሚሠጥ የእምነት ቃል፣ ፍርድ ቤት በራሱ ግንዛቤ ሊወስድባቸው የሚችሉ ጉዳዮች /Judicial notice/፣ የሕግ ግምት (presumption of fact) እና የመሓላ ቃል ሲሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 2024(መ) የተመለከተም ፍሬ ነገር ከማረጋገጫ ዘዴዎች ከሆኑት አንዱ መካከል ስለሕግ ግምት የተደነገገ ነው፡፡ የኪራይ ገንዘብን አስመልክቶ አልተከፈለኝም በሚል አከራይ ለሚያቀርበው ክርክር ተከሳሽ የሆነው ወገን ከፍያለሁ የሚል ክርክር የሚያቀርብ ከሆነ እና ያልተከፈለው ኪራይ ገንዘብ ሁለት ዓመት ጊዜ ያለፈው መሆኑ ሲረጋገጥ ፍርደ ቤቱ ኪራይ ገንዘቡ እንደተከፈለ ግምት የሚወስድበት ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሆኖ የሚቀርብ ሳይሆን በፍሬ ነገሩ ክርክር ሂደት በክሱ የተመለከቱ ጉዳዮች በፍሬ ነገር ማረጋገጫ ዘዴዎች የተረጋገጠ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች የሚከራከሩት ኪራይ ገንዘቡን ከፍለናል የሚል ሳይሆን ገንዘቡን የመክፈል በውል ሆነ በውርስ ሕግ አንገደድም የሚል በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ኪራዩ እንደተከፈለ የሕግ ግምት የሚወስድበት አግባብ የለም፡፡

በሀሉተኛ ደረጃ በ1ኛ ተጠሪ የቀረበው መቃወሚያ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው የሚል ነው፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5(1) መሠረት በሕግ ሥልጣን የተሠጠው ማናቸውም ፍርድ ቤት ክርክሩን ተቀብሎ የመጨረሻ ፍርድ ከሠጠ በኋላ ቀድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ሥረ-ነገርና የተያዘው ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነ፤ በክርክሩ ላይ የነበሩት ወይም ከተከራካሪዎቹ መብት ያገኙ ሦስተኛ ወገኖች በዚያው ነገር ሁለተኛ ክስ ማቅረብ አይችሉም፡፡ በድንጋጌው መሠረት ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ አልቋል ለማለት የተዘረዘሩት አራት መስፈርቶች በአንድነት መሟላት አለባቸው፡፡ የመጀመሪያው መስፈርት ጉዳዩን የተመለከተው <u>በሕግ ሥልጣን የተሠጠው</u> (ሠረዝ የተጨመረ) ማናቸውም ፍርድ ቤት መሆኑ ነው፡፡ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው የሚለው ትርጉም የሚያስፈልገው መስፈርት ነው፡፡ በፍርድ ቤት የሥረ-ነገር ሥልጣን ሳይኖረው የተሠጠ ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 212 እንደተመለከተው በይግባኝ እስካልተለወጠ ድረስ የጸና በመሆኑ ጉዳዩን አስቀድሞ ፍርድ እንደተሠጠበት የሚያስቆጥር ነው፡፡ ስለሆነም በሕግ ሥልጣን የተሠጠው የሚለው የሥረ-ነገርና አካባቢያዊ ሥልጣንን የሚመለከት ሳይሆን አስቀድሞ ጉዳዩ የታዬው በሕግ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ወይም ዳኝነት ነክ አካል መሆኑን ለማመላከት ነው፡፡ ይህም በፍርድ ቤት ሥልጣን ሳይኖረው ፍርድ መስጠት እንደ አስገዳጅ ውሳኔ የሚቆጠርና የሚፈጸም መሆኑን የሚያሳይ እና በኢትዮጵያ እንዳልተሰጠ የሚቆጠር ፍርድ (void judgment) እንደሌለ ያስረዳል፡፡ ዳኝነት ለመስጠት በሕግ ሥልጣን

ያልተሠጣቸው አካላት ጉዳዩ ላይ አስቀድመው በአስተዳደር ማየታቸው ሆነ ውሳኔ መስጠታቸው ጉዳዩን በፍርድ እንዳለቀ የማያስቆጥር እና ክርክር ከማድረግ የሚከለክል አይሆንም፡፡ ይህም በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 37 እና አንቀጽ 79(1) እንደተመለከተው የመዳኘት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች እና የዳኝነት ነክ አካል ብቻ መሆኑን የሚያሳይ እና በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 50(2) የመንግሥት አካላትን የሥልጣን ክፍፍል መርህን (principle of separation of powers) የተከተለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ሁለተኛው መስፈርት አስቀድሞ በፍርድ ቤት የተሠጠው የመጨረሻ ፍርድ መሆን አለበት የሚለው ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ክርክሩን አይቶ ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ እልባት ወይም ውጤት የሠጠበት መሆን እንዳለበት የሚያስረዳ መስፈርት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ በመሰማት ላይ እያለ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ሆነ በይግባኝ ደረጃ ላይ እያለ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 69(2)፣ አንቀጽ 70(መ) እና አንቀጽ 73 በተመለከተው አግባብ መዝገቡ ከተዘጋም፤ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74(1) እንደተመለከተው በተቋረጠው ጉዳይ አዲስ ክስ ማቅረብ መከልከሉ ጉዳዩ በፍርድ አልቋል የሚለውን መርህ የሚከተል ነው፡፡ በሌላ በኩል በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 231(1) የተመለከተው በክስ አቤቱታው የተገለጸው የማያስከስስ መሆን ወይም የሥረ-ነገር ሥልጣን አለመኖር ምክንያት ተደርጎ ክሱ መቋረጡ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ያልተሠጠበት ስለሆነ በፍርድ እንዳለቀ የሚያስቆጥር አይሆንም፡፡ የክስ ምክንያት ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ መኖሩን፣ የተጠየቀው ዳኝነት በፍርድ ቤት የሚዳኝ መሆን አለመሆኑን እና በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተመለከቱት ጉዳዮች ቢረጋገጡ የተጠየቀውን ዳኝነት ለከሳሽ ለመወሰን ህግ የሚፈቅድ መሆን አለመሆኑን መመርመርን የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህም የክስ ምክንያት የሌለው ጉዳይ የሚለው በዋነኛነት ዳኝነቱን ለመጠየቅ ከህግ የመነጨ ግንኙነት እያለው ግን በፍርድ ቤት ሊዳኙ የማይችሉ ጉዳችን (non-justiciable matters) የጉዳዩ ባሕሪ በፍርድ ቤት ሥልጣን ሥር ሊወድቁ የማይችሉ፣ አከራክሮ ሊፈጸም የሚችል ውሳኔ ሊሰጥባቸው የማይችሉ በመሆናቸውና ከሳሽ ወገን ክሱን ሲያቀርብ የጠቀሰው ወይም የገለጸው የክሱ መሰረት የሆነው ምክንያት በህግ የክስ መሰረት ሊሆን የማይችል ከሆነ የማያስከስስ ነው ተብሎ ክሱ ውደቅ የሚደረግበት ሥርዓት ነው፡፡ ጉዳዩም በሥረ-ነገሩ ታይቶ ውሳኔ ያላረፈበት በመሆኑ እንደ መጨረሻ ፍርድ የሚቆጠር አይደለም፡፡ የሥረ-ነገር ሥልጣን ባለመኖር ክሱ ውድቅ መደረጉም ሥልጣን ባለው ሌላ የዳኝነት አካል ጉዳዩ ቀርቦ ሊወሰን የሚችል በመሆኑና በሥረ-ነገሩ ጉዳዩ ላይ ውሳኔ ያልተሠጠበት በመሆኑ በፍርድ እንዳለቀ ጉዳይ ተቆጥሮ መቃወሚያ ሊቀርብበት የሚችል አይደለም፡፡ ስለሆነም የመጨረሻ ፍርድ የሚለው በሥረ-ነገሩ መታየትን መሠረት ያደረገ ቅድመ ሁኔታ መኖር እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ሦስተኛው መስፈርት አስቀድሞ ፍርድ ያረፈበት ጉዳይ ሥረ-ነገሩና ጭብጡ አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር አንድ ዓይነት መሆን አለበት የሚለው ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ጉዳይ አንድ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ፍርድ ቤቱ በጭብጥነት የመረመረው ጉዳይ አሁን በተያዘው ክርክርም በጭብጥነት ተይዞ የሚመረመር ከሆነ ውጤቱ አስቀድሞ ፍርድ ያረፈበት ይሆናል፡፡ ሥረ-ነገሩ ተመሳሳይ ሆኖ ነገር ግን የሚያዘው ወይም የተያዘው ጭብጥ የተለያዩ ከሆነ በተያዘው ጭብጥ ላይ የቀደመ ፍርድ ባለመኖሩ ጉዳዩ በፍርድ እንዳለቀ ሳይቆጠር ክርክሩ ቀጥሎ ፍርድ ሊያርፍበት የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ በሕጉ ላይ የተቀመጠው አራተኛው መስፈርት

የተከራካሪዎች ወይም ከተከራካሪዎች መብት ያገኙ ሦስተኛ ወገኖች ተመሳሳይ መሆን እና በእነርሱ መካከል ያለ ክርክር መሆኑ ነው። የዚህ መስፈርት መነሻ ፍርድ የአስገዳጅነት ሀይል ሆነ ውጤት የሚኖረው በተከራካሪዎች መካከል ብቻ ነው የሚል ነው። ከተከራካሪዎች ውጭ ፍርዱን በመያዝ መብት ማቋቋም ሆነ ማስፈጸም አይቻልም። ፍርድ ቤት ጉዳዩን የሚመረምረው ሆነ ፍርድ የሚሠጠው ከተከራካሪዎች መካከል የተሻለ መብት ያለው ማን ነው ከሚለው ነጥብ አኳያ ብቻ ነው። በጉዳዩ ላይ ያላቸው መብት በፍርድ ቤቱ ሳይመረመር እና የመደመጥ ሆነ የመከላከል መብታቸው ሳይከበር ተከራካሪ ያልሆኑ ወገኖች ላይ ፍርዱ አስገዳጅነት አለው ሊባል አይችልም። የተከራካሪዎች ተመሳሳይነት የሚለው ከተከራካሪዎች በሕግ ሆነ በውል መብት የተላለፈላቸውን ሦስተኛ ወገኖች የመብታቸው ምንጭ የቀድሞው ክርክር ላይ ተከራካሪ በሆኑት ወገኖች ልክ በመሆኑ በእነዚህ ወገኖች ላይም ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ እንዳለቀ የሚያስቆጥር ነው።

በተያዘው ጉዳይ መቃወሚያው የቀረበው 1ኛ ተጠሪ እና ከ2ኛ - 8ኛ ድረስ ያሉት ተጠሪዎች መካከል የንግድ ቤቱን አስመልክቶ ያደረጉት ክርክርና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 180343 ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ የንግድ ቤቱ የሟች ቅጣው መሸሻ የግል ሀብት ነው ተብሎ መወሰኑን መሠረት በማድረግ ነው። በዚህ ክርክር ውርስ ማጣራት ሂደትን ተከትሎ አመልካች የኪራይ ገንዘብ የጠየቀበት የንግድ ድርጅቱ የውርስ ሃብት መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ጭብጥ ሲሆን አሁን በሰበር ችሎት ደረጃ የተያዘው ጉዳይ ደግሞ የኪራይ ገንዘብ አከፋፈልን የሚመለከት በመሆኑ የጭብጥ ልዩነት ያለው ነው። በውርስ ክርክሩ አመልካች ባለመሳተፉና ሊሳተፍም የማይችል በመሆኑ የተከራካሪዎች ተመሳሳይነትም የለም። ሥለሆነም ጉዳዩ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5(1) መሠረት በፍርድ ያለቀ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም።

በሥረ ነገሩ አመልካች የኪራይ ገንዘብ እንዲከፈለው የጠየቀ ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ  በቀድሞ ወረዳ 05 ቀበሌ 12 የቤት ቁጥሩ 1165 የሆነ የንግድ ቤት ላይ አመልካች እና ሟች ቅጣው መሸሻ ባደረጉት የኪራይ ውል መነሻ የሚጠቀሙበት ሲሆን አመልካች የኪራይ ተመን ለማሻሻል በሕግ ባለው ሥልጣን መሠረት ከጥቅምት 30 ቀን 2004 ዓ/ም በኋላ ላለው ጊዜ በወር ብር 31,479.00 እንዲከፍሉ አድርጓል። በማሻሻያው ላይ ቅሬታ ቀርቦም ተቀባይነት ያጣ በመሆኑ የውል ማሻሻያው ተግባራዊ ይሆናል። በሕግ አግባብ የተደረገ ውል በተዋዋዮች መካከል በፍ/ሕ/ቁ. 1731(1) እንደተመለከተው እንደ ሕግ የሚቆጠር መሆኑ እና በፍ/ሕ/ቁ. 1785(2) መሠረት በውል ዓይነተኛ መጣስ ከሌለ በስተቀር መፈጸም እንዳለበት የተደነገገ መሆኑ ሲታይ በተቻለ መጠን ተዋዋዮች ባስተላለፉት መብትና ግዴታ ልክ ውሉን የመፈጸም ግዴታ አለባቸው።

ተከራይ የሆኑት አቶ ቅጣው መሸሻ ሕዳር 13 ቀን 2005 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ በመሆናቸው ከሚያዚያ 01 ቀን 2004 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም ድረስ ያለውን የኪራይ ገንዘብ ከነቅጣቱ ብር 2,311,503.59 ተጠሪዎች እንዲከፍሉ አመልካች ዳኝነት ጠይቋል። 1ኛ ተጠሪ ክፍያው አይመለከተኝም የሚሉት የውል ግዴታ አልገባሁም፣ የንግድ ቤቱ በፍርድ ቤት ክርክር የሟች የግል ሀብት ተብሏል፣ ውርስ አጣሪው ንብረቱን ተረክቦ እያስተዳደረው ነው በሚል ነው። 1ኛ ተጠሪ የሟች ቅጣው መሸሻ ባለቤት

በመሆናቸው ከባለቤታቸው ጋር የነበራቸው ጋብቻ በሞት እስኪፈርስ ድረስ በጋራ ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑ አልተካደም፤ ንብረቱ የባለቤታቸው የግል ቢሆን እንኳን የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 62(1) መሠረት ገቢው የጋራ ስለሚሆን በጋራ ለሚጠቀሙበት ንግድ ሥራ ወጪውንም በጋራ የመክፈል ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡ ጋብቻው በሞት ከፈረሰ በኋላም በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መካከል 1ኛ ተጠሪ በ10/05/2005 ዓ/ም እና በ08/08/2005 ዓ/ም ለአመልካች ያቀረቡት ጥያቄ ሆነ ከአመልካች ጋር በ09/08/2005 ዓ/ም ብር 547,287.13 ዕዳ ለመክፈል ያደረጉት ሥምምነት እና በውሉ መሠረት ብር 200,000.00 መክፈል መጀመራቸው በንግድ ቤቱ መጠቀማቸውን መቀጠላቸውን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ አመልካች የኪራይ ገንዘብ እስከጠየቀበት ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም ድረስ 1ኛ ተጠሪ በንግድ ቤቱ ላይ ከ2ኛ-8ኛ ድረስ ካሉት ተጠሪዎች ጋር  የውርስ ክርክር በማድረግ መቀጠላቸው መረጋገጡ ሆነ አመልካች ንብረቱን እንዲረከባቸው ኃላፊነትን ስለማውረድ ክስ ባላቀረበቡት ሁኔታ ንብረቱን ለውርስ አጣሪ አስረክቤያለሁ በሚል ለኪራይ ገንዘቡ ኃላፊ ልሆን አይገባም የሚለው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለሆነም በሥር ፍርድ ቤቶች 1ኛ ተጠሪ ለኪራይ ገንዘብ ኃላፊ ናቸው ተብሎ መወሰኑ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ከ2ኛ-8ኛ ድረስ ያሉት ተጠሪዎች የሟች ቅጣው ወራሾች በመሆናቸው የአባታቸውን ዕዳ እንዲከፍሉ የቀረበ ዳኝነት ነው፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከ2ኛ - 8ኛ ያሉት ተጠሪዎች በንግድ ቤቱ ላይ ወራሽነት ቢያረጋግጡም በንግድ ቤቱ ባለመጠቀማቸው ኃላፊነት የለባቸውም ብሏል፡፡ ከ2ኛ-8ኛ ድረስ ያሉት ተጠሪዎች የሟች አባታቸው ወራሽ ሲሆኑ አመልካች የኪራይ ገንዘብ የጠየቀበትን የንግድ ቤት ጨምሮ የውርስ ሀበት መውረሳቸውን ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 180343 የተሰጠው ውሳኔ ያስገነዝባል፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 826(1) መሠረት ሟች ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ ውርሱ የሚከፈት ሲሆን በንዑስ ቁጥር ሦስት እንደተመለከተው የሟች መብቶችና ግዴታዎች ወደወራሾች ይተላለፋሉ፡፡ ሟች አባታቸው የንግድ ቤት ከአመልካች በመከራየታቸው ምክንያት የሚመጣ ዕዳን ከ2ኛ-8ኛ ድረስ ያሉት ተጠሪዎች ወራሾች በመሆናቸው ብቻ ለዕዳው ኃላፊ ናቸው፡፡ በንግድ ቤቱ መጠቀም አለመጠቀማቸው በጭብጥነት የሚመረመር አይደለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ወራሾች መሆናቸውን አረጋግጦ እያለ በንግድ ቤት አልተጠቀሙም በሚል ለክሱ ኃላፊ አይደሉም በሚል የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

አመልካች ክፍያው ሳይፈጸም በመዘግየቱ ቅጣት እንዲከፈለው ጠይቋል፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 1790 እና 1791 እንደተመለከተው ውል ያልተፈጸመው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ውል ያልፈጸመው ወገን የደረሰውን የጉዳት ኪሣራ መክፈል አለበት፡፡ የሚከፈለው ኪሣራ ተዋዋዮች በፍ/ሕ/ቁ. 1889 መሠረት አስቀድመው የወሰኑት ከሆነ በውሉ የተመለከተውን መጠን ሲሆን ተዋዋዮች አስቀድመው ኪሣራውን ካልወሰኑ በክርክር ሂደት ፍርድ ቤት ኪሣራውን በማስረጃ አጣርቶ የሚወስነው ይሆናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት እስከ ስድስት ወራት ድረስ ያለውን የቅጣት ክፍያ 10% እንዲከፈል የወሰነ ሲሆን ቀሪ ቅጣት ክፍያውን ውድቅ ያደረገው በውሉ አንቀጽ 3(3) መሠረት ከስድስት ወር በላይ ክፍያ ቢዘገይ ውሉን የመሠረዝ መብት አመልካች እያለው መብቱን ሳይጠቀም ለተጠራቀመው ቅጣት ክፍያ እንዲከፈለው መጠየቅ አይችልም

በማለት ነው፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 1784 እና ከ1786-1789 መሠረት ውል በፍርድ ቤት ወይም በተናጠል በተዋዋይ ወገን ሊሠረዝ ይችላል፡፡ በውሉ የተመለከቱ ሁኔታዎች ሲሟሉ ተዋዋይ ወገን ውሉን በተናጠል የመሠረዝ መብት የሚኖረው ሲሆን ወሉን የመሰረዝ መብቱን አለመጠቀሙ እንደውል እንዲፈጸም ከመጠየቅ ወይም ውሉ ባለመፈጸሙ ምክንያት ጉዳት ሲደርስ ጉዳት ኪሣራ እንዳይጠይቅ የሚያደርግ አይደለም፡፡

አመልካች ውሉን የመሠረዝ መብት ባለመጠቀሙ የውል አፈጻጸም የቀጠለ እስከሆነ ድረስ እና ተጠሪዎች ክፍያ ሳይከፍሉ ለቆዩበት ጊዜ በውሉ የተመለከተው የጉዳት ኪሣራ/ቅጣት እንዲከፍሉ መጠየቁ ሕግን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 1893 እንደተመለከተው ዳኞች መቀጫ መቀነስ የሚችሉት ውሉ በከፊል ከተፈጸመ ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የኪራይ ውል ክፍያው በየወሩ የሚከፈል በመሆኑ እና ተጠሪዎች ከሚያዚያ 01 ቀን 2004 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም ድረስ ላሉት 57 ወራት ክፍያ ባለመክፈላቸው በየወሩ ለዘገየው ክፍያ በውሉ የተመለከተውን ቅጣት የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤት ቅጣት ክፍያው በከፊል ብቻ ነው ሊከፈል የሚገባው ሲል የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 194706 በጥቅምት 16 ቀን 2013 ዓ/ም እና በመዝገብ ቁጥር 195936 ታህሳስ 08 ቀን 2013 ዓ/ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 191209 ግንቦት 04 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. 1ኛ ተጠሪ እና ከ2ኛ - 8ኛ ድረስ ያሉት ተጠሪዎች ብር 2,311,503.59 በጋራ ለአመልካች እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲያስፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠው እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ